# የአቶ ሰለሞን ለሌ/ኮሎኔል ፍስሀ ደስታ ሙግስና በ SBS ሬድዮ

## አጭር ማብራሪያ

ነሲቡ ስብሐት (አሉላ)

ኅዳር 4 ቀን 2008 ዓ.ም. (November 14, 2015)

ሰላም ለሁላችሁ

ኅዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም. "ምነዋ ኢ.ሕአፓ ዴ (ኢ.ሕአፓ አንድነት?)" በሚል ለላኩት ጽሁፍ የተሰማችሁን ለፃፋችሁት አጠር ያለ ማብራሪያ እሰጣለሁ።

በቅድሚያ በጽሁፉ በግልጽ እንደተቀመጠው የአቶ ሰለሞን በSBS ሬድዮ በሰጡት ቃለ መጠይቅ እንዴት እነኚህን ወንጀለኞችና የስንቱን ቤትና ሀገር የዘጉ የደርግ ባለስልጣናትን ያወድሳል ነው እንጂ ስለሰጠው ውስጣዊ ዝርዝር አይደለም።

የኢ.ሕአፓ ዴ ቃል አቀባይ አቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴ በ SBS ሬድዮ ለፍስሀ ደስታ ያቀረቡትን ምስጋና በጽሁፍ እናንብበው። ሥርዝ የተጨመረበት።

*"በመጀመሪያ ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ  ሬድዮ ጣቢያው ይህንን እድል ለኢ.ትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ስለሰጠ። ሌተናል ኮሎኔል ፍሰሐ ደስታን በጣም ላመሰግን እወዳለሁ። ጊዜያቸውን ወስደው እስካሁን ከተፃፉት መጽሐፍት አንፃር በተለይም የደርግን ወገናዊነት አድርገው ከተነሱት አንፃር ትምህርታዊ ሊሆን የሚችልና በሚዛናዊነቱም ሚዛን የደፋ ብለን ልንጠቅሰው የምንችል መጽሐፍ በማቅረባቸው ላመሰግናቸው እወዳለሁ። አርአያም ይሆናሉ ብዬ አስባለሁ ሌሎች ለሚከተሉት ፀሐፊዎች። ከዚያ ጋር በተያያዘ እንግዲህ አንዳንድ ምናልባት ጊዜ ሳያገኙ ቀርተው ያላሰቧቸው በወጉ ወይም ደግሞ ያልተመለከቷቸው ነገሮች አሉ ብለን ስለምናምን እነዚያ ላይ ማስተካከያዎች ለመስጠትና እስቲ የሳቸውንም ሀሳብ በነዚህ ላይ እንግዲህ ተለዋጭ ሀሳቦች ስለምናቀርብ ምን እንደሚሉ ለማወቅም ጉጉ ነን ግን በእኛ በኩል ሦስት መሠረታዊ ሀሳቦችን በተለይም እሳቸው በዚህ ሬድዮ ጣቢያ በ SBS ካደረጉት ውይይት በመነሳት ሦስት መሰረታዊ ነገሮች ላይ ደግሞ የእኛን አስተሳሰብ ለመግለጽ እንወዳለን። . . ."* የጥቅሱ መጨረሻ።

አቶ ሰለሞን እኛ እያሉ ይህንን መግለጫ ሲሰጡ እራሳቸውን ሳይሆን ኢ.ሕአፓ ዴን መወከላቸውን "ይህንን ዕድል ስለተሰጠን" ብለው ነው የሚጀምሩት። በዚህ ጉዳይ አንድ ወንድሜ አባል እንዳልሆኑ ጠቅሰው ሊተቹኝ የፈለጉት የላኩትን የኦዲዮ ቅጅ ሰምተውታል፤ ግና ያዳመጡት አይመስለኝም።

አቶ ሰለሞን በኢ.ሕአፓ ዴ ስም "እስካሁን ከተፃፉት መጽሐፍት አንፃር…***ትምህርታዊ ሊሆን የሚችል…ሚዛን የደፋ…አርአያ ይሆናሉ…።***" እያሉ ያኾጎደጎዱት ምስጋና እውን ሲቪላይዝድ መሆን ነው?

እስቲ ከሌ/ኮሎኔል ፍስሀ ደስታ መጽሐፍ "አብዮቱና ትዝታዬ" አለፍ አለፍ እያልኩ ስለ ኢሕአፓ የጠቀሱትን ላስቀምጥ (ሥርዝ የተጨመረበት)፦

*"...በመዲናዋ አዲስ አበባ **ኢሕአፓ ቦዘኔዎች** አሰባስቦ የመንገድ መብራቶችን እንዲሰብሩና ለሽብር ሥራ እንዲደራጁ አደረገ።..."* **ገጽ** 195

*"...በየትምህርት ቤቱም **የጠረባ ቡድን** አቋቁመው ትምህርት ከድል በኋላ ባማለት ሲቀሰቅሱ የሚቃወማቸውን በመደብደብና **በጩቤ በመተልተል** ፍርሃትና ጭንቀት ላይ እንዲወድቁ አደረጉ።..."***ገጽ** 196

*"...ኢሕአፓ **ሥርዓተ አልበኝነቱን፣ የኢኮኖሚ አሻጥሩንና በሰሜኑ ክ/ሀገራት በማካሄድ ላይ የነበረውን የዘረፋና የተኩስ ድርጊት** ከማስተባበል ይልቅ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ "ጦርነት ታወጀብን" በማለት ደርግን ለመክሰስ ብሎም ወጣቱን በተሳሳተ መንገድ ለማጋፈጥና **ለማስጨፍጨፍ** ተሯሯጠ።..."* **ገጽ** 198

ከቅድመ ቀይ ሽብር በ1969 ዓ.ም. ሜይ ዴይን አስመልክቶ ሚያዝያ 21 ቀን የተካሄደውን ሰልፍና በትንሹ በአዲስ አበባ ብቻ ከ2000 በላይ ወጣቶችና ሕፃናት በደርግ ታጣቂዎች ያለቁበትን ሰላማዊ ሰልፍ ይቅርታ ጠይቁአለሁ ባዩ ኮሎኔል እንዲህ ያስቀምጡታል፡

*"መኢሶን ወደ ሥልጣን ለመውጣት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ መሆኑን የተገነዘበው ኢሕአፓም ሚያዝያ 22፡ 1969 ለአጸፋ ተነሳ። ወጣቱንና ልዩ ልዩ መሳሪያ፡ ተቀጣጣይ ፈንጂና የእጅ ቦምቦች የታጠቁ ሰኳዶችን በማሰማራት በአዲስ አበባ ከአራቱም ማዕዘናት **የደርግ ጽ/ቤትን ለመውረር** ተንቀሳቀሰ። መረጃው እንደደረሰም የፀጥታ ኃይሎች፣ ካድሬዎችና አብዮት ጥበቃዎች ሰልፉን ለመበተንና ለመግታት በየአቅጣጫው ተሰማሩ።..."* **ገጽ** 239

ከላይ ያስቀመጥኳቸው እጅግ ከብዙው ጥቂቱን "አብዮቱና ትዝታዬ" የሚለው የፋሽስት መንግስቱ ቀኝ እጅ የፃፉት መጽሐፍ በኢሕአፓ ላይ ከነዙት ውንጀላ ነው። እንግዲህ "***ትምህርት ሰጪ፣ ሚዛን ሚደፋ፣ አርአያ የሚሆኑ...***" እየተባሉ በኢሕአፓ ዴ ተሞገሱ።

**ውድ ወገኖች**!

በቀደም ጽሁፌ መጽሐፉን ያላነበባችሁ እንኳ ልትታዘቡ የሚገባችሁ የደርግ ነብሰ በላዎች በተለይ የሀገርና የሕዝብ ልጆች ደም በእጃቸው ያለ እውን እንዲህ ያውም የኢሕአፓን ስም በያዙና ስንት ተመክሮ አለን በሚሉ ያለአግባብ ሲወደሱ ያላሳፈረ ምን ሊያሳፍር።

የፋሽስቱን መንግስቱ ኃ/ማርያምን "ትግላችን" መጽሐፍ ከዚህ በፊት በፃፍኩት "ግድያችን" ብዬዋለሁ፣ የረዳቱን ዛሬም ባልደረቀው ፊርማው ስንቱን ሕፃናትና ወጣቶች "እርምጃው ይፈፀም" እያለ ያስገደለው የፍቅረስላሴ ወግደረስን መጽሐፍ "እኛና አብዮቱ" እንዲሁ "እኛና ባህሪያችን" ብዬው ነበር። "አብዮቱና ትዝታዬ" የሚለው ሦስተኛው የደርግ መጽሐፍ በፍስሀ ደስታ ሲወጣ ምንም ላይገኝበት ለማንበብም ስሜቱ አልነበረኝም። ያው የተለመደ "ኢሕአፓ

*መጀመሪያ ተኮሰብን፣ የሱማሌ ጦርነትን ከሲያድ ባሬ ጎን በመሆን በመደገፍ ጦሩ ስንቅ ውስጥ ጠርሙስ ፈጭቶ ከተተ፣ የኤርትራን በኢትዮጵያ ቅኝ መያዟን በመደገፍ ከሻቢያ ጋር ወገነ፣ ወዘተ*" ከዚህ ያልዘለለ የተለመደ ውንጀላና ማላዘን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ብገዛውም ለማንበብ መገፋፋቱ አልነበረም።

እንደው ይቅርታ ጠይቄአለው የሚለው የመጽሐፉ ማሻሻጫ ቃልን "ሆን ተብሎ" መጽሐፉን በመገምገም መልክ የተፃፉትን አሻሻጭ ጽሁፎችና በአንዳንድ መገናኛ ብዙሃንም ሲወራላቸው ማንበቡ አይከፋም በማለት ጀመርሁት። በአጭሩ የዛሬ 37 ዓመት ኢሕአፓ አባል በመባል የደረሰብኝ ግርፊያ ቀለለኝ። መላ ሰውነቴ ደማ፣ ውስጤ ተቃጠለ። ስለዚህ መጽሐፍ ምንነት ሕዝብ ማወቅ አለበት ብዬ የራሴን አስተያየት በማዘጋጀት ላይ እያለሁ ነው በፍስሐ ደስታ መጽሐፍ የኢሕአፓ ዴ መግለጫ በአቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴ የተሰጠውን ያደመጥኩት። እውን የማውቀው ሰለሞን ነው፤ ነው ያልኩት? እውን የኢሕአፓው ሰለሞን ነው ያልኩት?

እውን ይህ መጽሐፍ ኢሕአፓን በመስደቡና በመወንጀሉ፣ እነኚያን አንድ ብርቅዬ ትውልዶች መጨረሳቸው ሳያንስ ቦዘኔ፣ ነብሰ ገዳይ መባል "***ለሌሎች ፀሐፊዎች አርአያ የሚሆኑ ሰው***" ይባላል።

ኮሎኔል ፍስሀ ኢሕአፓንና ያንን ትውልድ እንዴት ሊመቱ እንደሚችሉ የተጠቀሙት ስልት በመግቢያው ላይ "*ደርግ በወሰዳቸው በጎ እርምጃዎች እንደምደሰት ሁሉ፤ በማወቅ፤ በድፍረት፤ ባለማወቅና በስህተት ለተፈጸሙት ደግሞ ሙሉ ሃላፊነት በመውሰድ፤ በበኩሌ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ።*" ያሉት አባባል ነው። መጽሐፉን ካነበባችሁ በኋላ ግና *ይቅርታው በአሰሳ፣ በነፃ እርምጃና በቀይ ሽብር የጨረሱትን የኢሕአፓ አባላትና ንጹሐን ዜጎች እንዳልሆነ መረዳት አይከብድም።*

በመጠኑ ከመጽሐፉ ቀንጭቤ ያስቀመጥኩላችሁ ኮሎኔሉ ኢሕአፓን እንዴት እንደወነጀሉ እየታየ "በርቱ" ከማለት አልፎ ሌሎች የደርግ ወንጀለኞችም እንዲጽፉ አርአያ ሆነዋል ማለት አያሳፍርም ወይ? ተብሎ ሲጠየቅ እንደ ወቀሳ የሚቆጠረው ምኑ ላይ ነው ወገን።

አሉላ በኅዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም. በለቀቅሁት ጽሁፍ የአቶ ሰለሞንን ስለ ኤርትራ፣ ሱማሊያና ደርግ ስለሰጡት ችግር አለኝ ብዬ አላነሳሁም። ***ያ ትውልድንና ኢሕአፓን እየወነጀለና ቦዘኔ፣ ነብሰ ገዳይ፣ ቅጥረኛ እያለ የተፃፈ መጽሐፍ በኢሕአፓ ዴ እንዴት ይወደሳል ነው።*** ግልጽ ላድርግና። ለዚህም መድረኩ ላይ የቀረቡት አቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴ ናቸውና ስማቸው መነሳት ግዴታ ነው። እሳቸው በድርጅታቸው ስም ተሰድቦና ተወንጅሎ የተጻፈበትን ኢሕአፓ ፀሐፊውን በአደባባይ ለማሞገስ ያልከበዳቸው የእኔ ዑ ዑ ዑ ታ ክብደቱ ምኑ ላይ ነው?

ለማክበር ከሆነ በግለሰብ ደረጃ አቶ ሰለሞንንም ሆነ ማንንም የማከብር ነኝ። የተሳሳተ መስሎ የታየኝን ጉዳይ ላይ ብዕሬን የማነሳው የጉዳዩ ከባድነት ነው። ዛሬ ኢሕአፓንና ያንን ትውልድ እየቀጠቀጡ እያየሁ ከመከላከል ወደ ኋላ አልልም። አቶ ሰለሞንም እውን መጽሐፉን አንብበው ከሆነ ይሄን ምስጋና ሊያቀርቡ የፈለጉት እስቲ ያልገባኝ ይኖራልና

ለሌሎቻችንም ትምህርት ይሆን ዘንድ ስላደነቁት የኮሎኔል ፍስሀ መጽሐፍ የሌሎችን ገምግመው እንዳስነበቡን ሁሉ ስለዚህም ይጻፉልን።

አቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴ በSBS ሬድዮ ለሌ/ኮሌኔል ፍስሐ  የሰጡት ሙግስና በአንድ በኩል ለደርግ አባላትና ለፀሐፊው እጅግ ጠቀሜታ ሲኖረው በሌላ በኩል ደግሞ "ኢሕአፓ ወጣት አስጨረሰ" እየተባለ ሁሌ ለሚሰማው የዛሬ ወጣት "ይኸው እውነት ቢሆን አይደል እንዴ የኢሕአፓው መሪ እንኳን ያሞገሱት" እንደሚያሰኝ አንጠራጠር። ኮሎኔል ፍስሐም ከአንድ ታዋቂ የኢሕአፓ ሰው ይህን ሙግስና ሲያገኙ እንዴት ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ መገመት የሚያቅት አይመስለኝም።

በeedn መወያያ መድረክ ሀሳባችሁንና አስተያየታችሁን ለሰጣችሁኝ (አስተያየቶቹ አባሪ ተደርጎ ተያይዟል) በሙሉ ምስጋናዬን እያቀረብሁ ጠቅለል ባለ መልኩ ትንሽ ምላሽ ልስጥ፦

**ወንድሜ አበራ**

ምሬት ካልከው አሉላ ለምን "የምሬት" አፃፃፍ ሊጽፍ ቻለ ብለህ ለመጠየቅ በጣም ቀላል ነው። መጽሐፉን ማንበብ ብቻ በቂ ነው። ሌላውን ጉዳይ ትተህ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ችሎታህን ብታውለው ላልከው ጥሩ ምክር ነው። ግና ታሪካችን ሲዛነፍ ሲበላሽ ያቅሜን የማደርገውን መከላከል አትጥላው። ስለ ኢትዮጵያ አንድነትም እስቲ በሻቢያ በኩል የተያዘው ሩጫ በረድ ይበል እስካሁን የተጣላሁት ይበቃል የጊዜ ብርሃን ሲፈነጥቅ ብቅ እላለሁ ብዬ ነው። ደራሽ ውኃን ቆም ብሎ ማሳለፉ ይጠቅማልና ነው።

**ወገን አርአያ አምሳሉ**

አንተም እንደጻፍከው በአቶ ሰለሞን/ኢሕአፓ ዴ የሬድዮ መግለጫ የተሰጠው የመጀመሪያው አንድ ደቂቃ ምስጋና ነው ችግሬ። ቀላል እንዳይመስልህ! ከላይ በጽሁፍ ያቀረብኩት ረጋ ብላችሁ እንድታነቡት ነው። በመቀጠል ስለ አቶ ሰለሞን ማንነትና የትምህርት ደረጃ አሳውቀኸኛል፤ አመሰግናለሁ። እኔ በዚህ ጽሁፌም ሆነ በሌላ ሌሎችን በጥቅሉም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ስም ጠቅሼ ስጽፍ ስለ ሙያቸው ስላላቸው የትምህርት ደረጃ አከብራለሁ። በፖለቲካው መስክ እገሌ ድግሪ አለው፣ ዶክተር ነው፣ ከ12ኛ ክፍል አልዘለለም ወዘተ ብዬ የማበላልጥ አይደለሁም። እኔም የምጽፌው ሀሳብ ለሠፊው የኅብረተሰብ ክፍል እንዲዳረስ፣ እንዲገባና ግልጽ እንዲሆን ብዬ ነውና የትምህርት ሙያዬና ማንነቴ የስህተቴ መሸፈኛ ሊሆን አይገባም። በማቀርበው፣ በምጽፈው፣ በማደርገው ውይይት ሌላም ሌላ ልተችም ሆነ ልደገፍ የሚገባኝ ተምሯል፣ አልተማረም ተብሎ አይደለም። አደባባይ ወጥተን ስንናገር ስንጽፍ ሙያችንን ወደ ጎን አድርገን ቢሆን ይመረጣል። የእሱ ቦታ እራሱን የቻለ ነውና።

በመጨረሻም አቶ ሰለሞን የኢሕአፓ ዴ ቃል አቀባይ መሆኑን ከቃለ መጠይቁም ኢሕአፓ ዴን ወክሎ እንደሆነ መረዳት ትችላለህ።

**ወገን አቶ ሰለሞን** **(shewanew sheyedo)**

*ለእኔ ኢ.ሕአፓ ዓላማ ነው። የዛሬ 40 ዓመት የተነሳሳው ለሰው ልጆች እኩልነት፣ ለሰው ልጅ ያልተገደበ መብት፣ ለሀገራችን አንድነትና ሉዓላዊነት፣ ለሰንደቅ ዓላማችን ክብር፣ ለሕዝብ መንግሥት ምስረታ ውስጤን ቆስቁሶት ወደ ትግል የገባሁባቸው ዓላማዎች ናቸው። እነኚህን ዓላማዎች ማንም ይዟቸው ቢነሳ በዚያ ጥላ ሥር ሆኘ ምታገል ነበርኩ። አዎ ኢ.ሕአፓ ይህንን ዓላማ አንግቦ ብቅ በማለቱ የተቀላቀልነውና እስከ ሕይወት መስዋዕትነት የተከፈለው ለዚህ ዓላማ ነው። እኝያ ከጎናችን እያየናቸው የወደቁት ወንድም እህቶቻችን ለዚህ ዓላማ የተዋደቁና የተሰዉ ናቸው። እነኚህን ሰማዕታት ሳነሳ ኢ.ሕአፓ ዋናው ነውና የምሟገተው። በየቦታው የወደቁ ወገኖቻችን ታሪክና ስማቸው እንዳይበከል የሙታን ዓጽም ይወቅሰናልና ነው። በወደቁት ሰማዕታት ውስጥ ደግሞ በርካታ አዛውንቶች፣ የትላንት ሕጻናት የዛሬ ጎልማሶች ምነው የሚያያቸው ጠፋ? አስታዋሽ አጡ? እንዳይባል የምንችለውን ከማበርከት ባሻገር በትውልዱ ላይና በኢ.ሕአፓ ላይ የሚደረገውን ውርጅብኝ ልክ አይደለም ብዬ ስከላከል ህያው ለሆነው ዓላማ ብዬ እንደሆነ ግልጽ ላደርግልህ እወዳለሁ።*

**ወገን ጌድዮን**

*"አብዮቱና ትዝታዬ" መጽሐፍን በማንበብህ የተሰማህንና የእኔንም ሀሳብ በመጋራት ላቀረብከው ጽሁፍ አመሰግናለሁ። ሌሎችንም የምለው ፍርድ ከመስጠት በፊት እየቆሰላችሁም ቢሆን አንብቡት። ከላይ እንዳስቀመጥኩት ኮለኔሉ መጽሐፋቸው እንዲሸጥና የኢ.ሕአፓ ውንጀላ እንዲሰምርላቸው የረቀቀ ዘዴ ተጠቅመዋል። ለዚህ ደግሞ ተባባሪዎች በደንብ አድርገው አራግበውላቸዋል። ይህን የተረዳህ ይመስለኛል። ከፃፍከው ውስጥ የምስማማው እኔም "አቶ ሰለሞን በእርግጥ ይህንን መጽሐፍ አንብቦታል ወይስ በተወራው ነው የሄደው" ጥያቄ ከቶኛል። በርግጥ ከላይ እንደተቀመጠው አቶ ሰለሞን መግቢያው ላይ መጽሐፉን እንዳነበበ ሆኖ ሲያሞግስ ይደመጣል። ቀጠል አድርጎም "እሳቸው በዚህ ሬድዮ ጣቢያ በ SBS ካደረጉት ውይይት በመነሳት..." ይላል። ፍስሀ ደስታ በSBS ሬድዮ በሰጡት ላይ ተንተርሶ ከሆነ አቶ ሰለሞን ምላሽ የሰጠው ያላነበበው መጽሐፍ ላይ ሙግስና ምን አስኬደው ይባላል። አንብቦትም ከሆነ ሌላውን በሆዱ ይዞና ሙግስናውን ትቶ ስለ ተጠየቀው ሦስት ነጥቦች ብቻ ቢያወሳ መልካም ነበር።*

<u>**ወገን መንግስቱ**</u>

*የፃፍከው እኮ እኔም ያልኩት ነው። ለማውራትና ሊታመን በማይችል መንገድ ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ በደርግ የተካሄደ ጅምላ ጭፍጨፋ ከየካቲት 12ቱ የጣሊያን ጭፍጨፋ ቀጥሎ በባሰ መልኩ አንድ ትውልድ ያጠፋ ነው። አንዳንድ ጊዜ ግራ የሚለኝ የቀይ ሽብርን ምን ያህል አስከፊ ሰቆቃ እንደነበር ውስጡ ካልነበርህ ለመረዳትና ለማመን የሚከብድ ይመስለኛል። ትንሽም የቀይ ሽብርን ጠብታ ቢያሳይ ብዬ ስለ ከፍተኛ 15 የቀይ ሽብር እውነተኛ ታሪክ "**በፍፁም ነው እምነቴ**" መጽሐፌ አሳይቻለሁ ብዬ እገምታለሁ። ከዚህ የበለጠ መጽሐፍ በመቶዎች በተፃፈ ነበር። ግና ደርጐቹ በልጠውናል። እና "**ትምህርት ሰጪ፣***

*አርአያ የሚሆኑ፣ ጊዜዎን ወስደው...*" እየተባሉ እኚህ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰብን ሕይወት የቀጠፉ ዛሬ አርባ ዓመት ሞልቶታል ተብሎ ቢተዉ እንኳ ታሪኩ ሊዛባ ይገባዋልን? እና ወንድሜ አቶ ሰለሞንማ የድርጅቱን ኢሕአፓ ዴን አቋም እንደ ፓርቲው ቃል አቀባይነቱ ነው የሰጠውና ከሱ ለማጣላት የሚደረገውን ሙከራ ወደ ጐን እንግፋውና ማብራሪያ ይሰጥበት እስቲ። በግልህ ልጠይቅህና እስቲ አቶ ሰለሞን ለሌ/ኮሎኔል ፍስሀ ደስታ የሰጠው ሙግስን እውን ልክ ነው ትላለህ?

ነሲቡ ስብሐት (አሉላ)

ቸር ይግጠመን።

አስተያየት የሰጡ ወገኖች አባሪ ቀጥሎ ባሉት ገጽ ይመልከቱ።

## **<u>አባሪ</u>**

### ኅዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም. "ምነዋ ኢሕአፓ ዴ (ኢሕአፓ አንድነት?)" በሚል ለላኩት ጽሁፍ በeedn መወያያ መድረክ ሀሳባቸውንና አስተያየታቸውን የሰጡ ወገኖች

### <u>Araya Amsalu</u>

selam Alula,

I think you wasted two pages and God knows how much time on your former comrade, instead it would have been better if you focused your time and energy to critique the book by Fisseha Desta.

I know Solomon Ejigu Gebreselassie, he is a dedicated patriot with a rational mind. For me, a person who was infatuated by EPRP as a child, is a bright spot in a rather disappointing intellectual and moral standard displayed by many of my former idols. You keep calling the group "Ato Mersha Yoseph's group, Is that your way of belittling the other intelligent comrades? Knowing Solomon, he will not join a group unless he believes in it. It is worth to mention a bit about Solomon's background:
- HSIU 3rd year in Social Science
- Bachelor of Science in Petroleum Engineering - USA
- Bachelor of Arts in Philosophy - USA

Also Solomon was elected by the EPRA members to the provisional Committee that replaced the EPRP leadership on the field. (hence his nick name ጊአኮ)

My advice to you, as your younger brother, focus your energy on real enemies of our freedom. Keep up the good work chronicling the deeds of your comrades.

Thank you

Araya Amsalu

selam,

I forgot to mention this in my last posting, please listen to the audio, it takes only about 20 minutes. Thank you Alula for the link. Solomon refuted three allegation made by Col Fisseha Desta about EPRP, nay, he dismantled them!.
BTW, I wonder if you stopped listening after a minute and half? Yes, he was polite and recognized some good pints raised by the Colonel but he was very forceful in his defense of EPRP's positions then.

Thank you
Araya

## Solomon (shewanew sheyedo)

Selam Dr. Araya Amsalu,

I am wondering why you are defending indefenesable people Solomon G/Selassie I was with Solomon from Assimba to Chiliga and to Gedarife.

I know Solomon G/Selassie in EPRA especially In Assimba and in Chiliga. When four members of the EPRA leadership left the army (Dawit Seyum, Yemane, Roba and Gazu) without any information to EPRA members Solomon G/selassie and ohers were asigned by EPRP as temporary leadrs of EPRA. untill the election .

Here are some of the bad things Solomon and some of his friends did to EPRA

1. When EPRA had problems in Cheliga we were asked to have a seminar The committee to conduct the seminar were (Kiflu Tadess, Solomon G/selassie and four others we started the seminar in Chako then they pulled us through Quara and took us to a place called Shinfa at the boarder of Ethiopia and the Sudan. From there we were left alone. From Shinfa we moved to Amerakoba from Amrakoba some of us moved to Gedarif.

2 We stayed for few months in Gedarif, then Solomon and his abelij distributed a paper called " Death to EPRP, death to Tsegaye death to Iyasou"

You can find this paper on Assimba web page.

3 When we were in the USA this is especially very important. EPRP called all its old members and started organizing we were going forward, What happened that time Mersha wanted to sign an affidavit and join the TPLF/ EPRDF, most of the leadership members didn't agree with Maresha's position then they decided to send both positions to the members, majority of the members opposed

Meresha Solomon and few others created organization within organization. 7 years ago when the especial congress was called and when we started the congress the Anja group walked out from the congress and formed EPRP (D) The rest of us continued our congress and elected our leadership passed resolution including to create a committee to follow and create communication between those who walked out and the EPRP. am I clear Dr Araya?, Nesibu also walked out with these people. here i am not supporting Nesibu

EPRP is only one and only one

Long live Ethiopia

Long live PERP

Solomon

**Abera Sisay**

Selam Alulla, Dr Araya and All
I know what Alulla went through during the Derg era. For that reason, I know how Alulla is going to react when it comes to anyone with past connection with the Derg. Although I understand where he is coming from, I wish Alulla invest his time in something new. Alulla has amazing writing skills and he is a committed advocator for Ethiopia in general. I read Alulla's paper posted today titled Solomon Vs Fisiha. I then listened to Solomon's interview and tried to see where the problem was. Solomon's argument on Fisiha's book is very civilized and we all should encourage such arguments. Solomon told fisiha what we and Alulla think of the Derg. The only difference is Solomon used new approach with civilized manner to express our position. I agree with Dr Araya that Solomon defended EPRP with civilized manner. We need to reconcile our old but painful differences with others if we are truly serious in bringing true democratic society in Ethiopia. Thank you for posting Solomon's arguments. I enjoyed it.
Abera Sisay

**Araya**

selam Dr Solomon,

I hope you are not going back in time to color your experience with Solomon because of your recent disagreement. As for the story of EPRA's liquidation in 1979, I have heard so many sides of the story, I can say it has as many sides as the story tellers. Hopefully someday soon we will get an unbiased story. One thing I know for sure is when I came to the USA in 1991, few years later when I met him on the Internet - Solomon was back in the party.

Now, have you listened the interview Alula criticized, he provided a link? I listened to it, if I stopped at the 2 minutes mark I would have taken the same position as Alula. Solomn went ahead and dismantled point by point Col Fisseha's arguments regarding EPRP. I do not think Solomon needs my defense, he is more than capable of defending himself. He used to be a member of EEDN in the old days, I am not sure if he is still a member. I do not see why he would be condemned for defending the reputation of your common heritage.

Thanks
Araya

**ጌዲዮን (ፍራንክፈርት )**

ሰላም አሉላ ፣ አበራ እና ሌሎችም

እኔም የአቶ ሰለሞን ገብረ ሥላሴን ቃለ መጠይቁን በጽሞና አዳምጨዋለሁ። ምንም እንኳን የአቶ ሰለሞን አቀራረብ ብረዳውም ለፍሰሃ ደስታ የተደረገው ምስጋና ትንሽ የተጋነነ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ምስጋናውን በማንጋጋት የፍሰሃ ደስታ ደጋፊዎቹ ሊያሰራጬት የፈለጉትን የጅምላ ይቅርታ መልዕክትን ማጋነን እንዳይሆን እፈራለሁ። በበኩሌ የጅምላ ይቅርታ ጥየቃን አላምንም። ለምንድነው ይቅርታ የተጠየቀው ? የትኞቹ ስህተቶች ናቸው በግል የተፈጸሙት ? የሚለውን ያላካተተ ነገርግን በጅምላ የተጠየቀ ይቅርታ ውጤት አልባ ነው ብዬ አምናለሁ።

ከአቶ ሰለሞን ቃለ መጠይቅ የተረዳሁት የፍሰሃ ደስታን መጽሐፍ እንዳላነበቡት ነው። እኔ እንደማምነው ቢያነቡት ኖሮ አቀራረባቸው የተለየ ይሆን ነበር። ቢያነቡት ኖሮ በመጽሐፉ ውስጥ ብዙ ሊጠቀሱ የሚችሉ ስህተቶች ባልገደፏዋቸው ነበር። መጽሐፉን አንብቤዋለሁ የሚሉ ከሆነ ግን የዘመነ ደርግን ዕውቀታቸውን ጥያቄ ውስጥ ያስገባል ። እኔ እስከማውቃቸው ድረስ ለብዙዎቹ የኢሕአፓ አመራር ምስሌ እስከመሆን የሚደርስ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው ይመስለኛል ።

ብዙ ሰዎች መጽሐፉን ሳያነቡ ስለመጽሐፉ የተሰጠውን ግምገማ ብቻ በመመልከት ወይም በኢሳት የተደረገውን ቅስቀሳ በመስማት ወይም ደግሞ ፍሰሐ ደስታ በአውስትራሊያ ሬዲዮ የሰጡትን ቃለ መጠይቅ ብቻ እንደ በቂ በመውሰድ ስህተት እየሰሩ እንደሆነ ተረድቻለሁ። የአቶ ሰለሞን ምንአልባት በአውስትራሊያ ራዲዮ ለፍሰሃ ደስታ ለተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ብቻ መልስ ይመስላል። በዚህም ምክንያት ብዙዎችን ሊያናድድ ችሏል ። ንዴት ደግሞ ሃይለ ቃልን ስለሚፈጥር ተሰሚነትን ያሳጣል። የአሉላ ስህተት እዚህ ላይ ነው ። ከመልዕክቱ በላይ ንዴቱ ጮኸ። አላስፈላጊ አልነበረም።

ወደፊት በሰፊው እኔም እንደ አሉላ የምመለስበት የፍሰሐ ደስታ መጽሐፍ በውስጡ ብዙ ራስን ለመከላከል ሲባል ሌሎችን የመወንጀል ተግባር ያየሁባቸውን ቦታዎች አንስቼ ከሌሎች የደርግ አባላት የተጻፉት ጋር በማነጻጸር አንድ አነስተኛ ጽሁፍ ለማቅረብ ሃሳብ አለኝ ። ለምሳሌ ያህል ፍሰሐ ደስታ( አብዮቱና ትዝታዬ ገጽ 191) በርበሬ ደብቃችኋል ተብለው የፍየል ወጠጤ የተፈከረባቸው ነጋዴዎች የኢሕአፓ የኢኮኖሚ አሻጥረኞች በማለት ለመወንጀል መሞከርና መገደላቸው ትክክል ነበር ብሎ ለማሳመን መጻፍ ምንያህል አስከፊ እንደሆነ መረዳት ካቃተን የሚገርም ነው ። ነጋዴዎቹ ከኢሕአፓ ጋር በተያያዘ ሳይሆን ብዙ ገንዘብ ለማትረፍ ያደረጉት ጥረት እንደነበር የሚታወቅ ነው። በዘመኑ ደርግ የተጠቀመበትን ፕሮፖጋንዳ ዛሬም እንደ እውነት መጻፍ ነውረኝነት ነው። ለእነዚህ ነጋዴዎች ቤተሰቦች 500 ብር ለማይሞላ በርበሬ አባተህን ገደልኩ ብሎ መፎከር መቼም አሳፋሪ ነው ። ቢሆንስ ለፈረሱላ በርበሬ የሰው ሕይወትን ማጥፋት ዛሬ ትክክል ነው ተብሎ መታመን የለበትም። ለነገሩ ኢሕአፓ አዲስ አበባ ውስጥ በሰፊው ተንቀሳቀሰ አልተንቀሳቀሰ የደርግ ዘመን የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በረሃብ የሚታወስ እንጂ በብልጽግና የማይታማ ነበር ። ታዲያ ምኑ ላይ ነው የፍሰሃ ደስታ ይቅርታ ? አቶ ሰለሞንንም ያስደሰታቸው ይቅርታ መጽሐፉን ቢያነቡት ኑሮ ይቅርታውን ፈልገው ያጡት ነበር።

ይቅርታ ይቅርታ ጠያቂና ተጠያቂ ሲኖር ብቻ ነው ይቅርታው የሚሠራው። ንጹሃንን ከገደሉ በኋላ በመወንጀል በሰፊው በመጽሐፉ ልባድ ላይ ይቅርታ ብሎ መመጻደቅ ያሳፍራል። ስለ ይቅርታ አደራርግና እርቅ በሚመለከት ዓለም አቀፍ ልምዶች ማየትም የተገባ ይሆናል ።ቢያንስ የደቡብ አፍሪካን። ፍስሃ ደስታ ይቅርታ መጠየቃቸው ትክክለኛ መንገዱን መያዛቸው ሊሆን ይቻላል። ነገር ግን በመጽሐፋቸው ውስጥ ታሪክን በማጣመም የራስን ወንጀል ወደ ሌሎች ማዛወር ከቀይ ሽብር የባሰ ዳግም ወንጀል ነው ። ይህ ደግሞ መጽሐፉ ውስጥ ጎልቶ ይታያል። ፍሰሐ ደስታ ያልተሳተፉበትን ሲያስጮኹ ፣ የተሳተፉበትን በሹክሹክታ ሲያልፉ ይስተዋላል ። በጽሁፍ የተገኙ የደርግ መረጃዎች ብዙ የማናውቀውን ጉዳይ አስተምረውን አልፈዋል። ወደፊትም ፍሰሃ ደስታ የቱ ጋ ታሪክን ራስን ለመከላከል እንዳጣመሙ ለሕዝብ ማሳወቅ ያሻል።

ኢሕአፓ ( አንድነት ) ወይም ቃል አቀባዩ አቶ ሰለሞን መግለጫ ወይም ቃለ መጠይቅ ከመስጠታቸው በፊት ጠለቅ ያለ ጥናት መደረግ እንደነበረበት እኔ በበኩሌ አምናለሁ። ጉዳዩ የታሪክ ነውና ቢቻል ብዙዎችን የሚያካትት ውይይት ያስፈልግ ይሆናል። ይቅርታውስ ተቀባይነት አለው ወይ ? የሚለው ጥያቄ መመለስ ይኖርበታል።

አቶ ሰለሞን ገብረ ሥላሴን ደግሜ መጽሐፉን እንዲያነቡት እያሳሰብኩ ለዛሬው እዚህ ላይ ጽሁፌን እገታለሁ ። ይህ ጽሁፍ ለአቶ ሰለሞን እንደደርስ ብታደርጉልኝ ደግሞ ታላቅ ትብብር እንዳደረጋችሁልኝ እቆጥራለሁ ።

ከሰላምታ ጋራ

ጌዲዮን (ፍራንክፈርት )

**Abera Sisay**

Selam Gedion and all, I too did not read the book. My point was about being civilized on our arguments . We can be productive when we argue in a civilized manner . Otherwise, our points will be shadowed by our negative approach. Based on the interview given by Solomon, he defended EPRP in three major issues . Thanking the writer is simply a norm in a civilized society even if you disagree. For me, I believe in a new way of arguing on issues . Our style has to change if we want to be heard. That is how I saw it.
Sent on the new Sprint Network

***መንግስቱ***

***ሰላም ነሲቡ ወንድሜ***
***የኮሎኔሉን መጽሀፍ አላነበብሁም እና ስለይዘቱ ደግፌም ሆነ ተቃውሜ መናገር አልችልም። ግን የወንድማችንን ቃለመጠይቅ ሙሉን አዳምጫለሁ። እንደአንድ የደርግ ተጠቂም እና የግፉ ተካፋይ ሁሉ እነዚህ ወንጀለኞች በህይወት ኖረው ታሪካቸውን ለማሳመር መሞከራቸው እጅጉን ያስቆጨኛል። በቂመኝነትና በቀል ጠንስሼ ሳይሆን በመቶሽህወች የቀጠፏቸው የትውልዴ አባላት ደም ከዚህ በላይ ፍርድ ስለሚፈልግ ነው። ይህን ካልሁ በኋላ ወንድም ነሲቡን መተቸት አልፈልግም ግን በወንድማችን በሰለሞን ላይ የተወረወረው ትችት በሁለት ጉዳይ ተገቢ አይደለም ባይ ነኝ።***

**1-** ***ጅራፍ እራሱ ገርፎ እንዲሉ ያን የታገለ ትውልድ ገዳዩ ፋሽስት በሶማሊያ ጦርነት ተባባሪ ነው በማለት ለዘመናት ያካሄደው ፕሮፖጋንዳ አውቀው በሚያደናቁሩ ሲስተጋባ እናያለን። ይህን አስመልክቶ ሁሉም የፋሽስቱ ግልገሎችም ሆኑ የቀይ ሽብሩ ተዋንያን ቢደጋግሙት የሚገርም አይደለም። አጋጣሚውን በመጠቀም በአንድ የሬዲዮ ቃለምልልስ ወንድም ሰለሞን ሁሉም እንዲያዳምጠው በሚመጥን ተገቢውን መልስ ሰጥቷል ባይ ነኝ። እናም በእርሱ የተወረወረው ወቀሳ ከልክ እላፊ ነው ብየ አምናለሁ።***

**2-** ***ሌላው የፍጅቱን አጀማመር አስመልክቶ የሚነሳው ጉዳይ ነው። ደርግ የተባለ ቡድን ገና ከጠዋቱ በትረ ስልጣኑን በጨበጠበት ቀን ያወጀውን ማስታወስ በቂ ነበር። እንዳለ እድል ሆኖ የታጋይን ቅስም መስበር። ከቻሉም መግደልና ስም ማርከስ ከማይጮ መልስ ባንዳ እና ስደተኛ ለሹመትና ለስልጣን ሲዳረግ። አርበኞች አንገታቸው ለገመድ አልያም ግዞትና እንግልት እንደተሰጣቸው የቅርብ ታሪክ ሆኖ በደርጎችና የእነርሱ አሽከሮች የተቀዳ ተምሳሌ በመሆኑ ደርግ ቀይ ሽብርን የደም ጠርሙስ ወርውሮ ከማወጁ ሁለት አመታት በፊት ግድያውን በቀድሞ ሚኒስትሮች እንደጀመረው አሌ አይባልም። ድፍን* **1967-68** *ነጻ እርምጃ የተባለው ዜጎችን ያለፍርድ መግደሉ ዘግናኙ ታሪካችን ነው። ኢሕአፓ እርሳን መከላከል የጀመረው* **1969** *ሕዳር ነበር። ይህ ደግሞ ቢዘገይ እንጅ ከደርግ የቀደመ አልነበረም። ደግሞም በአይነቱም ሆነ በይዘቱ የተለየና እራስን ከነጻው እርምጃና ቀይ ሽብር መከላከል ያለፈ ተግባር አልነበረም። ይህን ወንድማችን ሰለሞን በተገቢ መልሷል። ለሰው በሚገባ ቋንቋም አስረድቷል። ከዚህ በተረፈ የቀረ ካለ ቀሪውን መሙላቱ የእያንዳንዳችን የዚያ ግፍ ቀማሾች ሀላፊነት ይመስለኛል። ደግሞም መጽሀፉን እገመግማለሁ ብሎ ያደረገው ስራ አልነበረም እና በዝርዝር አልሄደበትም። ስለተጠየቀ ተገቢውን መልስ ስጥቷል ባይ ነኝ።***

***ነሲቡም ሆነ፤ ወንድም ጌዲዮን እንዲሁም ቀሪወቻችን የነዚያን አገር ገዳዮች ማንነትና ምንነት ማጋለጥ። የሚጽፏቸውን በነቂስ አሳይቶ መተቸት ተገቢ ስለሆነ ትኩረታችንን ወደዚያ ብናዞር መልካም ይመስለኛል። ዛሬ ታጋይን ማዋረድ እንኳን እኛ ተጨምረንላቸው እነርሱ አፋሽ አጎንባሽ አግኝተው እየዘመቱብን አይደለም? በራስ ላይ ዘመቻውን እረገብ ብናደርግ ይሻላል እላለሁ።***
***ከትህትና ጋር***

*መንግስቱ*